የኮቪድ-19 ክትባት

# እውነታዎቹን ያግኙ።

## የማጠናከሪያ መርፌዎች





## የኮቪድ-19 ክትባቶች ውጤታማ ናቸው

የኮቪድ-19 ክትባቶች ከከባድ ህመም፣ ሆስፒታል ከመተኛት እንዲሁም ከሞት ይከላከላሉ። ብቁ ሲሆኑ የማጠናከሪያ ክትባቶች መውሰድን ጨምሮ፣ የኮቪድ-19 ክትባቶችን ወቅታዊ ማድረግ ከቫይረሱ ይበልጥ ጥብቃ ለማግኘት አስፈላጊ ነው።

## ማጠናከሪያዎች ደህንነታቸው የተረጋገጠ ነው

የኮቪድ-19 የማጠናከሪያ ክትባቶች (ቡስተሮች) ከመጀመሪያው ክትባቶች ጋር አንድ አይነት ንጥረ ነገር ያላቸው እና በመቶ ሚሊዮኖች ለሚቆጠሩ ሰዎች ደህንነታቸው የተረጋገጠ ነው። መለስተኛ የጎንዮሽ ጉዳቶች የተለመዱ ናቸው። ከባድ የጎንዮሽ ጉዳቶች በጣም አልፎ አልፎ የሚከሰቱ ናቸው።





## ማጠናከሪያዎች ደህንነትዎ ተጠብቆ እንዲቆይ ይረዱዎታል

ማጠናከሪያዎች ከኮቪድ-19 እንደተጠበቁ ሆነው መቆየት እንዲችሉ ሙሉ በሙሉ ከተከተቡ በኋላ የሚከተቡት ክትባቶች ናቸው።



የማጠናከሪያ (ቡስተር) ክትባቶች ከብዙ ክትባት ዓይነቶች ጋር አብረው የሚሰጡ እና የተለመዱ ናቸው። ለምሳሌ፣ የቲታነስ ክትባቶች በየ 10 ዓመቱ ለአዋቂዎች ማጠናከሪያ ክትባቶች ያስፈልጋቸዋል።

የሳይንስ ሊቃውንት አንዳንድ ክትባቶች የሰዎች የበሽታ የመከላከል አቅም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ እንዲሄድ እንደሚያደርጉ ደርሰውበታል፣ እናም የማጠናከሪያ ክትባቶችን መውሰድ ከበሽታ ተጠብቀው እንዲቆዩ ይረዳቸዋል። የኮቪድ-19 ማጠናከሪያዎች በተመሳሳይ መንገድ ይሠራሉ።

NRC-RIM
National Resource Center for Refugees, Immigrants, and Migrants



ለበለጠ መረጃ፦ cdc.gov/coronavirus

# የማጠናከሪያ ክትባትን ማን ሊከተብ ይችላል

የማጠናከሪያ ክትባቶች ለሁሉም ሰዎች ተጨማሪ ደህንነት ይሰጣሉ፣ ነገር ግን በተለይ የጤና ችግሮች፣ የሥራ ወይም የኑሮ ሁኔታ ችግር ላለባቸው ሰዎች፣ ይህም ማለት በኮቪድ-19 የመያዝ ወይም በጠና የመታመም እድላቸው ከፍተኛ ለሆነ ሰዎች በጣም አስፈላጊ ናቸው፡፡

የኢሚግሬሽን ሁኔታዎ ምንም ይሁን ምን እንዲሁም የጤና መድህን ወይም መታወቂያ ቢኖርዎትም ባይኖርዎትም የማጠናከሪያ ክትባቶች ለሁሉም ሰው ነፃ ናቸው፡፡



## የበለጠ ጥበቃ ያግኙ

እራስዎን፣ ቤተሰብዎን እና ማህበረሰብዎን ከኮቪድ-19 ለመጠበቅ ምርጡ መንገድ ክትባቶችዎን ወቅታዊ ማድረግ ነው፡፡ ክትባትን ወቅታዊ ማድረግ ማለት ሁለቱንም የባለ ሁለት-መርፌዎች ክትባት ዶዞችን መውሰድ እና ከዚያም እርስዎ ብቁ የሆኑባቸውን ማንኛውንም የማጠናከሪያ ክትባቶች መከተብ ማለት ነው፡፡

የሁሉንም ሰው ደህንነት ለመጠበቅ ጭንብል መልበስዎን ይቀጥሉ፣ አካላዊ ርቀትን ይጠብቁ እና ሲታመሙ ቤት ይቆዩ፡፡

# ራስዎን ይጠብቁ፡፡ ማህበረሰብዎን ይጠብቁ፡፡ ይከተቡ፡፡

NRC-RIM
National Resource Center for Refugees, Immigrants, and Migrants

ለበለጠ መረጃ፦ cdc.gov/coronavirus